የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ.ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ ከተማ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et


ቀን/DATE: መስከረም 04 2019

ቁጥር/REF NO. 1/256/04/19

ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ: <u>መመሪያ መላክን ይመለከታል</u>

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ለመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት አሰያየምን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1146/2018 አዘጋጅቶ ያጸደቀና በሥራ ላይ እንዲውል ያደረገ መሆኑ ይታወቃል::

ስለሆነም ተቋማችሁ የመመሪያውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን የፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት አሰያየም ሂደት እንድትፈጽሙና ተግባራዊ እንድታደርጉ እያሳሰብን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1146/2018 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆናችንን እንገልጻለን::

ከሰላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

ግልባጭ

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአስተዳደርና መሰረተ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ
- ለህግ አገልግሎት ስራ አስፈጻሚ

<u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>

# ለመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት አሰያየምን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1146/2018

ትምህርት ሚኒስቴር

ሐምሌ /2018 ዓ.ም

# መግቢያ

በዩኒቨርሲቲ ማህበረሰቡ ቅቡልነት እና የሥራ ተነሳሽነትን ለመጨመር፣ ብሎም ተቋማዊ ብቃትን ለማሳደግ መልካም አስተዳደርን ማስፈን የሚያስችል የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ስየማ ብቃትን መሰረት ያደረገ እና ውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን አሳታፊ እና ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለውን የከፍተኛ አመራር የኃላፊነት ቦታዎች ብዝሃነት እና ሁሉን አሳታፊ የሆነ ውድድርና ምደባ ማካሄድ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሪፎርም ሥራዎች በመከናወን ላይ በመሆኑ፣ በሙያው የሰለጠኑ፣ ብቃትና ችሎታ ያላቸው እንዲሁም እምነት የሚጣልባቸውን አመራሮች ወደ አመራርነት በማምጣት የትምህርት ጥራት እና ተገቢነትን ለማሻሻል ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ (5) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት አሰያየምን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1146/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1/ "ከኢንዱስትሪ ለሚመጡ" ማለት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውጪ ባሉ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች ውስጥ በበላይ እና በከፍተኛ ኃላፊነት እንዲሁም በዚህ ደረጃ ባሉ የሥራ መደቦች ላይ ያገለገሉ አመራሮችን የሚያካትት ነው፤

2/ "የአመራር እና አስተዳደር የሥራ መደቦች" ማለት በአዋጁ የተገለፁትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ዋነኛ ዓላማዎች ተፈፃሚ ለማድረግ ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሾሙባቸው የሥራ መደቦች ናቸው፤

3/ ከዚህ በላይ ከተተረጎሙት ቃላት ውጭ በመመሪያው ውስጥ ያሉ ቃላት በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 በተገለፀበት አግባብ ትርጓሜ ይኖራቸዋል፤

4/ በወንድ ጾታ የተገለፀ አገላለፅ የሴትንም ያካትታል።

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ተጠሪነታቸው ለትምህርት ሚኒስቴር በሆኑ እና ራስ-ገዝ ባልሆኑ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለፕሬዚዳንትነት እና ለምክትል ፕሬዚዳንትነት የሥራ መደቦች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ።

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለውን አመራር ምልመላ፣ መረጣ እና አሰያየም ፍትሃዊ፣ ግልፅ፣ ብዝሀነት እና ተአማኒነት ያለው የውድድር ስርዓት መዘርጋት ነው።

## 5. መርሆዎች

የምልመላና መረጣ ሂደቱ የሚከተሉትን መርሆዎች የተከተለ ይሆናል፡-

1/ ግልፀኝነት

2/ አሳታፊነት

3/ ውድድርን መሰረት ያደረገ

4/ ብቃትና ችሎታን መሰረት ያደረገ

5/ ፍትሐዊነት

6/ ብዝሀነት

7/ ተጠያቂነት

8/ ሚስጥር ጠባቂነት

## ክፍል ሁለት

## የፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ምልመላ፣ መረጣና አሰያየም

### 6. የምልመላና መረጣ አጠቃላይ ሂደት

1/ ለውድድር የወጣውን ክፍት የኃላፊነት የስራ መደብ ማስታወቂያ በሁሉም የሚዲያ አማራጮች ማለትም በህትመት፣ በሚይንስትሪም እና ማህበራዊ ሚዲያዎች ተደራሽ ይደረጋል፤

2/ ማስታወቂያው ለተከታታይ 22 የስራ ቀናት አየር ላይ እንዲውል ተደርጎ የውድድሩ ምልመላ፣ መረጣና ስየማ ሂደት በሦስት ወር እንዲጠናቀቅ ተደርጎ በድምሩ በአራት ተከታታይ ወራት ውስጥ ተጠናቆ ውጤቱ ይገለፃል፤

3/ ብቁና በቂ የሆኑ ተወዳዳሪዎችን ለማግኘት የዕጩ አፈላላጊ ኮሚቴው ብቃትና ልምድ ያላቸው አመልካቾች ለውድድሩ እንዲመዘገቡ የማግባባትና የማበረታታት ሥራ ይሰራል፤

4/ አወንታዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተወዳዳሪዎች በሲቪል ሰርቪስ የሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1353/2017 መሰረት ተፈፃሚ ይደረጋል።

### 7. ለውድድር ጥቆማና ምዝገባ የሚያበቁ ጠቅላላ መስፈርቶች

1/ እጩ ተወዳዳሪው በሙስና፣ ሥልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ወይም በሌሎች ከባድ ወንጀሎች እና ከባድ የዲሲፕሊን ጉድለት ክስ ወይም ጥፋት የሌለበት መሆን አለበት። ሆኖም ግን የዕጩውን ታማኝነትና የሥራ ሥነ-ምግባር በቀጥታ የማይነኩ የፍትሐብሔር ክርክሮች ወይም መደበኛ የፍትሐብሔር ክሶች ከውድድር አያግዱትም።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእምነት ማጉደል፣ በከባድ የሙስና ወንጀል ወይም ከተቋሙ የኃላፊነት ባህሪ ጋር በቀጥታ በሚጋጭ ሌላ ከባድ ወንጀል በፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለ ማንኛውም ሰው ቅጣቱን ቢጨርስም ወይም በምሕረት ቢለቀቅም ለፕሬዚዳንትነትም ሆነ ለምክትል ፕሬዚዳንትነት መወዳደር አይችልም። ከተጠቀሱት ወንጀሎች ውጪ በሆኑ ሌሎች ወንጀሎች የተቀጣ ሰው መወዳደር የሚችለው የቅጣት ማገገሚያ (የስም ማደስ) ጊዜው በሕግ አግባብ ሲጠናቀቅ ብቻ ይሆናል።

3/ የዲሲፕሊን ቅጣት ተጥሎበት የነበረ ተወዳዳሪ በውድድሩ መሳተፍ የሚችለው የዲሲፕሊን ቅጣት ጊዜው ተጠናቆ በሕጉ መሠረት ነጻ ሲሆን ብቻ ነው።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

4/ በወጣው ክፍት የአመራር ስራ መደብ ላይ ከዚህ በፊት በማንኛውም የመንግስት ዩኒቨርሲቲ በተከታታይ ሁለት ተርም ያላገለገለ መሆን አለበት።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው የሁለት ጊዜ የአገልግሎት ገደብ ቢኖርም፣ በፕሬዚዳንትነት በተከታታይ ሁለት ጊዜ ያገለገለ አመራር በምክትል ፕሬዚዳንትነት የሥራ መደብ ላይ መወዳደር ይችላል።

6/ በምክትል ፕሬዚዳንትነት ለተከታታይ ሁለት ተርም ያገለገለ ሰው ለፕሬዚዳንትነት የሥራ መደብ መወዳደር ይችላል።

7/ ለወጣው ክፍት የአመራር ሥራ መደብ የጡረታ ጊዜው ሳይደርስ ለፕሬዚዳንት ሙሉ ስድስት ዓመት እና ለምክትል ፕሬዚዳንት 4 ዓመት ማገልገል የሚችል መሆን አለበት።

8/ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከአካዳሚክ ስታፍ ለሚመጣ እጩ ተወዳዳሪ የረዳት ፕሮፌሰርነት እና ከዚያ በላይ የአካዳሚክ ማዕረግ ያለው መሆን አለበት።

9/ ሁለተኛ ዲግሪ ኖሯት ከከፍተኛ ትምህርት ለምትመጣ ሴት እጩ ተወዳዳሪ የአካዳሚክ ማዕረግ ሳይጠበቅባት ለፕሬዚዳንትነት እና ለአስተዳደርና ቢዝነስ ልማት ም/ፕሬዚዳንትነት ክፍት የአመራርነት መደቦች ልትወዳደር ትችላለች።

10/ እጩ ተወዳዳሪው ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ መሆን አለበት።

11/ በአንድ ተቋም ውስጥ በፕሬዚዳንትነት ወይም በምክትል ፕሬዚዳንትነት (ወይም በምክትል ፕሬዚዳንትነት ማዕረግ) በመሥራት ላይ ያለ አመራር፣ በራሱ ተቋም በሚወጡ ተመሳሳይ የውድድር መደቦች ላይ መወዳደር አይችልም። ሆኖም በሌሎች ተቋማት በሚወጡ ክፍት የአመራር መደብ ማስታወቂያዎች ላይ መወዳደር ይችላል።

12/ ወደፊት አግባብነት ያለው የአክሪዲቴሽን ሥራ ከተጀመረ በኋላ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሃገር ሙሉ አክሪዴትድ ከሆኑ እና ታዋቂ ከሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች የተመረቀ መሆን አለበት።

13/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ የተቋሙን ራዕይና ተልዕኮ የሚያስፈጽም ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይኖርበታል። ይህ ስትራቴጂክ ዕቅድ የሚዘጋጀውና የሚቀርበው ተቋሙ በሚጠቀምበት መደበኛ የማስተማሪያ ቋንቋ ይሆናል ።

14/ ካምፓሱ ዩኒቨርሲቲው ካለበት ዋናው ግቢ 25 ኪሎ ሜትርና በላይ ርቀት ያለው ከሆነ እና ካምፓሱ በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና የተከፈተ ከሆነ የካምፓስ ኃላፊ በም/ፕሬዚዳንት ማዕረግ እንደሆነ ታሳቢ በማድረግ በወጡ ክፍት የካምፓስ የኃላፊነት የስራ መደብ ላይ በም/ፕሬዚዳንት መወዳደሪያ መስፈርት መሰረት እንዲወዳደር ይደረጋል።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

15/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና ባላቸው የኒቨርሲቲ ማስተማሪያ ሆስፒታሎችና እና የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ክፍት የኃላፊነት ቦታዎች ላይ በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ በዚህ መመሪያ መሰረት እንዲወዳደሩና እዲሰየሙ ይደረጋል።

## 8. ለፕሬዚዳንትነት ውድድር ብቁ የሚያደርጉ ልዩ መስፈርቶች

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 7 የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ ኖሮት የረዳት ፕሮፌሰርነት ወይም በሕክምና ሙያ ስፔሻሊቲና በዚህ ደረጃ አቻ የሆነ የአካዳሚክ ማዕረግ ያለው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው መደበኛ መርህ ቢኖርም፣ ሁለተኛ ዲግሪ ኖሯት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለምትመጣ ሴት እጩ ተወዳዳሪ የአካዳሚክ ማዕረግ (ረዳት ፕሮፌሰርነት) ሳይጠበቅባት ለፕሬዚዳንትነት የሥራ መደብ ልትወዳደር ትችላለች፤

3/ ዝቅተኛው የሥራ ልምድ በፕሬዚዳንትነት 2 ዓመት ወይም በምክትል ፕሬዚዳንትነት 3 ዓመት ወይም በኮሌጅ ዲንነት 3 ዓመት ያገለገለ መሆን ይኖርበታል።

4/ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚመጣ ተወዳዳሪ በአመራርነት የስራ መደብ በሰራበት መስሪያ ቤት የመራው የሰራተኞች ብዛት፣ ያመነጨውና ያስተዳደረው የበጀት መጠን ከሚወዳደርበት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመጣጣኝ መሆን ይኖርበታል፤

5/ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚመጡ እጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቀው ዝቅተኛ የስራ ልምድ በበላይ አመራርነት ቢያንስ 5 ዓመት፣ በከፍተኛ አመራርነት ቢያንስ 5 ዓመት፣ በዋና እና ምክትል ዋና ዳይሬክተርነት ወይም በዋና ስራ አስፈጻሚነት እና ከዚህ ጋር አቻ በሆኑ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ቢያንስ 8 ዓመት አገልግሎት የሰጠ/ች መሆን ይኖርበታል።

## 9. ለአካዳሚክ ጉዳዮች እና ለምርምርና ማህበረሰብ ጉድኝት ምክትል ፕሬዚዳንትነት ውድድር ልዩ መስፈርቶች

ከላይ በአንቀጽ 7 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል፡-

1/ የሦስተኛ ዲግሪ (ፒ.ኤች.ዲ) የትምህርት ዝግጅት ያለው እና ቢያንስ ረዳት ፕሮፌሰር የሆነ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

2/ በምክትል ፕሬዚዳንትነት 2 ዓመት ወይም በኮሌጅ ዲንነት ወይም በአካዳሚክ ዘርፍ በዳይሬክተርነት 3 ዓመትና ከዚያ በላይ የሰራ፤

3/ ለአካዳሚክ ጉዳዮች እና ለምርምርና ማህበረሰብ ጉድኝት ም/ፕሬዚዳንትነት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ከኢንደስትሪው የሚመጡ ተወዳዳሪዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቢያንስ ለ10 ዓመት የማስተማርና የምርምር ልምድ ያለው፤

4/ በአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሰው ለአካዳሚክ ጉዳዮች እና ለምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንቶችም ያገለግላል።

## 10. ለአስተዳደርና ቢዝነስ ልማት ምክትል ፕሬዚዳንትነት ውድድር ልዩ መስፈርቶች

ከላይ በአንቀጽ 7 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1/ ሁለተኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ የትምህርት ዝግጅት ያለው ሆኖ፣ ለወንድ እጩ ተወዳዳሪ ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም፣ ሁለተኛ ዲግሪ ኖሯት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለምትመጣ ሴት እጩ ተወዳዳሪ የረዳት ፕሮፌሰርነት አካዳሚክ ማዕረግ ሳይጠበቅባት መወዳደር ትችላለች።

3/ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚመጣ ተወዳዳሪ በአመራርነት የስራ መደብ በሰራበት መስሪያ ቤት የመራው የሰራተኞች ብዛት፣ ያመነጨውና ያስተዳደረው የበጀት መጠን ከሚወዳደርበት የከፍተኛ ትምህርት የአስተዳደርና ቢዝነስ ልማት ዘርፍ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ፤

4/ በአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሰው ለአስተዳደርና ቢዝነስ ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ውድድርም ያገለግላል።

## 11. ለፕሬዚዳንት እጩ ተወዳዳሪዎች የሚሰጥ የነጥብ አሰጣጥ ሥርዓት

1/ በአመራር መረጣ የትምህርትና አካዳሚክ ማዕረግ ደረጃ 30 ከመቶ፣ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅትና አቀራረብ 40 በመቶ እና የሥራ ልምድ 30 ከመቶ ክብደት እንዲይዝ ተደርጎ ውጤቱ ከ100% የሚሰላ ይሆናል ።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

2/ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ሆነ ከኢንዱስትሪ ለሚመጡ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር የትምህርትና የሥራ ልምድ ነጥብ አሰጣጥ በዚህ መመሪያ አባሪ 2 በተቀመጠው ሰንጠረዥ መሠረት ይፈጸማል ፡፡

3/ የስትራቴጅክ ዕቅድ ዝግጅትና አቀራረብ (40 ከመቶ) እጩ ተወዳዳሪው ያዘጋጀውን ስትራቴጅክ ዕቅድ ለተሳታፊዎች እና በመልማይና መራጭ ኮሚቴው በማቅረብ፣ በሚከተሉት ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት ተገምግሞ በመልማይ እና መራጭ ኮሚቴው ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ሀ) የአገር አቀፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች እውቀት (5 ነጥብ)፤

ለ) ስትራቴጂክ እቅዱ ከዩኒቨርሲቲ ራዕይ፣ ተልዕኮና የትኩረት መስክ ጋር የተያያዘ እና ግቦቹ የሚለኩ ስለመሆናቸው (5 ነጥብ)፤

ሐ) የዩኒቨርሲቲው አሁናዊ ችግሮችና እድሎች በግልጽ ተተንትነው ስለመቅረባቸው (5 ነጥብ)፤

መ).በስትራቴጂክ እቅዱ ላይ ግልጽ የሀብት ማመንጨት፣ ማስተዳደርና ዘላቂነት ከማረጋገጥ አንጻር በትክክል ስለመመላከቱ (5 ነጥብ)፤

ሠ) በስትራቴጂክ እቅዱ ላይ የተጠቃሚ ውጤት እና ተፅዕኖ በትክክል ስለመገምገሙ (5 ነጥብ)፤

ረ) የከፍተኛ ትምህርት የሪፎርም አጀንዳዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በእቅዱ ላይ የተመላከተ ስትራቴጂ ስለመኖሩ (3 ነጥብ)፤

ሰ) የከፍተኛ ትምህርት አለማቀፋዊነት እድሎች እና ተግዳሮቶች በትክክል ተተንትነው ተቋሙን አለማቀፋዊ ተወዳዳሪ ለማድረግ የነደፈው ስትራቴጂ (5 ነጥብ)፤

ሸ) ተቋሙን በቴክኖሎጂ ከማዘመን ረገድ የተቀየሰ ስትራቴጂ (4 ነጥብ)፤

ቀ) ለዝግጅት ገለፃ አቀራረብ ያለው ብቃት፣ ሙሉነት እና ግልጽነት (3 ነጥብ)ይሰጣል፡፡

4/ የስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅትና አቀራረብን ውጤት አሞላልን በተመለከተ የመልማይና መራጭ ኮሚቴ አባላት በተዘጋጀው ዝርዝር የውጤት መሙያ ቼክ ሊስት መሰረት በእያንዳንዱ መስፈርት በግላቸው የሰጡትን ነጥቦች በመደመርና በገምጋሚዎች ብዛት በማካፈል የሚገኘው አማካይ ውጤት ለተወዳዳሪው የሚሞላ ይሆናል፡፡

5/ በእጩ ተወዳዳሪዎች ከሚቀርበው ስትራቴጂክ እቅድ ጋር በተያያዘ፣ በኮሚቴው ከተወከሉት ሁለት የሴኔት አባላት ውጭ ሌሎች የሴኔት አባላት አጠቃላይ አስተያየት ከመስጠት በቀር ነጥብ አይሰጡም፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## 12. አሸናፊ ፕሬዚዳንት የሚመረጥበት ሂደት

1/ መራጭና መልማይ ኮሚቴው ከላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት ተወዳዳሪው ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት ከመቶው ተሰልቶ ብልጫ ያመጡ የአምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር በውጤታቸው ቅደም ተከተል መሰረት ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል።

2/ የመልማይና መራጭ ኮሚቴው ለይቶ ከመግለጫና ከቃለ ጉባኤው ጋር ያመጣቸውን አምስት ፕሬዚዳንታዊ ዕጩዎችን ሙሉ ሰነዱን በማያያዝ ቦርዱ ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀርባል።

3/ ሚኒስቴሩ ከቦርዱ የቀረቡለትን አምስት የፕሬዚዳንት ዕጩዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ ውጤታቸውን አደራጅቶ ለቦርዱ መልሶ ይልካል። (አባሪ 4 ይመልከቱ)

4/ ቦርዱም ከሚኒስቴሩ የቀረቡለትን አምስት ዕጩዎች በተሟላ ምልአተ ጉባኤ ቃለመጠየቅ በማድረግ በውጤታቸው ቅደም ተከተል መሰረት አብላጫ ውጤት ካመጡት ውስጥ ሦስቱን በመምረጥ ከምክረ ሐሳብ ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

5/ ሚኒስቴሩም ቦርዱ ካቀረበለት ሦስት ተወዳዳሪዎች መካከል አንዱን መርጦ በፕሬዚዳንትነት ይሰይማል።

## 13. የምክትል ፕሬዚዳንት ምርጫና አሰያየም

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 እና 10 ላይ በተጠቀሱት ልዩ መስፈርት እና በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል " ሀ " እስከ " ቀ " ያሉ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የእጩ ተመዳዳሪዎች ውጤት በመልማይ ኮሚቴው ይሞላላቸዋል ።

2/ መልማይና መራጭ ኮሚቴው ተወዳዳሪዎቹ ከመቶ ባላቸው ውጤት መሰረት ሦስት ብልጫ ያመጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በመለየትና በውጤታቸው ቅደም ተከተል በመዘርዘር ለስራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል።

3/ ቦርዱ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት ያመጣውን ዕጩ ከፕሬዚዳንቱ አስተያየት ጋር በማገናዘብ አንዱን መርጦ ይሰይማል።

# ክፍል ሦስት

## የኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

## 14. እጩ ተወዳዳሪ አፈላላጊ ኮሚቴ ስለማቋቋም



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

1/ ለፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንትነት ክፍት የሥራ መደቦች የሚቀርቡ ዕጩዎችን ለመመልመልና ለመምረጥ የሚያስችል "የእጩ ተወዳዳሪ አፈላላጊ ኮሚቴ" (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ መመሪያ መሠረት ተቋቁሟል።

2/ ቦርዱ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቃት ያላቸው የፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶችን ክፍት የሥራ መደቦች ብቁና በቂ ተወዳዳሪዎች ለማግኘት የሚያስችል አራት አባላት ያሉት የእጩ ተወዳዳሪ አፈላላጊ ኮሚቴ በኃላፊነት ያደራጃል።

3/ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለቦርድ ይሆናል።

4/ የኮሚቴው የአገልግሎት ጊዜ አንድ የአመራር ክፍት የስራ መደብ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ አሸናፊው እስከሚታወቅበት ጊዜ ድረስ ይሆናል።

5/ የእጩ ተወዳዳሪ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት አወቃቀር እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከአካዳሚክ ዘርፍ አንድ ------------------ ሰብሳቢ

ለ) ከኢንዱስትሪው ዘርፍ አንድ ----------------------------------------_-- አባል

ሐ) ከምርምር ተቋማት አንድ ---------------------------------------------አባል

መ) ከቀድሞ ዩኒቨርስቲ ምሩቃን አንድ ------------------------------------ አባል

15. የእጩ ተወዳዳሪ አፈላላጊ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1/ ለተወዳዳሪነት የሚፈለጉት ግለሰቦች ሲለዩ ስለ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተልዕኮ በጥልቀት የተረዱ፣ ብቃትና ልምድ እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤

2/ የአፈላላጊ ኮሚቴው አባላት ለተወዳዳሪነት ከሚለዩት ተጠቃሚ ግለሰብ ጋር ምንም አይነት የዝምድናና የጥቅም ግንኙነት ካለ ጥቆማ አለማድረግ፤

3/ ማስታወቂያ ለወጣባቸው የኃላፊነት ቦታዎች ብቃት ያላቸዉን እጩ ተወዳዳሪዎች ማፈላለግ፣ መለየትና እንዲያመለክቱ ማበረታታት፤

4/ እጩዎችን በሚያፈላልጉበት ወቅት የሴቶችን ተሳትፎ እና አካታችነትን ከግምት ውስጥ ማስገባት፤

5/ ኮሚቴው በእጩ አፈላላጊነት ሂደት ውስጥ የሚያገኛቸውን ማንኛውንም የግል መረጃዎች እና የኮሚቴውን የውስጥ ውይይቶች በሚስጥር መያዝ፤

6/ የእያንዳንዱን እጩ ተወዳዳሪ የለዩበትን ዝርዝር ምክንያት የያዘ የመጨረሻ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ፤

7/ እጩዎችን ለማግኘት የተጠቀሙባቸውን መንገዶች እና የግንኙነት መዝገቦችን ለግልጽነት ሲባል አደራጅቶ መያዝ።

16. የምልመላና መራጭ ኮሚቴ አወቃቀር

1/ የመልማይና መራጭ ኮሚቴ አባላት መምረጫ መስፈርቶች እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) ስራውን ለመስራት ፈቃደኛ መሆናቸውን በጽሁፍ የገለጹና አቅም ያላቸው፤

ለ) መልካም ስነ ምግባር ያላቸው፤

ሐ) ኃላፊነታቸውን በሙሉ ቁርጠኝነት፣ በፍትሀዊነትና በሀቀኝነት የሚወጡ፤

መ) ሚስጥር የሚጠብቁ፤

2/ የተቋሙ ቦርድ ሰባት አባላት ያሉት የመራጭና መልማይ ኮሚቴውን በኃላፊነት ያደራጃል።

3/ የኮሚቴው አባላት ውክልና እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ከቦርድ የሚወከሉ አንድ አባል -------------------------------------- ሰብሳቢ

ለ) ከሴኔት የሚወከል ሁለት አባል (አንዱ ሴት)---------------------------- አባል

ሐ) ከተማሪዎች ህብረት የሚወከል አንድ አባል ---------------------------- አባል

መ) የመምህራን ማህበር ተወካይ አንድ አባል ----------------------------- አባል

ሠ) ከትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ስራው ከሚመለከተው ክፍል አንድ ተወካይ ------------------------------------------------አባል

ረ) ከዩኒቨርሲቲ ውጭ ካሉ የሳይንስና የምርምር ተቋማት አንድ አባል -------- አባል

ሰ) ከተቋሙ የብቃትና የሰው ኃብት ልማት አስተዳደር ሰራተኞች የሚወከል አንድ አባል -- አባልና ፀሐፊ (ድምጽ አልባ)

4/ በሥራ ላይ ያሉ የዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች በዕጩ መልማይና መራጭ ኮሚቴ አባልነት አይወከሉም።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

5/ የዕጩ መልማይና መራጭ ኮሚቴ የአገልግሎት ጊዜ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ሲያጠናቅቁ በደብዳቤ የሚሻሩ ይሆናል።

## 17. የምልመላ እና መራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1/ መልማይ ኮሚቴው ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ለስራው አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎችን አደራጅቶ በአግባቡ መሰነድና መጠቀም፤

2/ የምርጫ ሂደቱን ዕቅድ እና የጊዜ ሰሌዳን ያዘጋጃል፤

3/ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ማስረጃዎች፣ ሰነዶች እና መረጃዎችን በሀርድ ኮፒ እና በሶፍት ኮፒ አደራጅቶ መያዝ፤

4/ የምልመላና መራጭ ኮሚቴው ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች መካከል ዝቅተኛውን መስፈርት የሚያሟሉትን ይለያል፤

5/ የስትራቴጂክ እቅድ መገምገሚያ ዝርዝር ቢጋር በማዘጋጀት ሚስጥራዊነቱን ጠብቆ እና በቦርድ አጸድቆ ወደ ተግባር መግባት፤

6/ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ውጤት ይሰጣል፤ መረጃውንም አደራጅቶ ይይዛል።

7/ በምርጫ ሂደቱ ላይ በቅሬታ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን በመቀበል ማጥራትና ማስተካከል፤

8/ የፕሬዚዳንት እና የምክትል ፕሬዚዳንቶች ምርጫ ሂደት ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ግልጽ እንዲሆን ማድረግ፣

9/ ለውድድር የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን በውጤታቸው መሰረት በደረጃ በመለየት አምስት ብቁ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ለቦርድ ከመግለጫ ጋር ማቅረብ፤

10/ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በሚለይበት ወቅት ብቃት ያለው ተወዳዳሪ ወይም በቂ ቁጥር ማግኘት ካልተቻለ፣ ምክንያቱን በመግለጽ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለቦርዱ ማቅረብ።

11/ ሌሎች ከቦርድ የሚሰጣቸውን ስራዎች ያከናውናል፤

12/ የምርጫ ሂደቱንና ውጤቱን የሚመለከት አጠቃላይ ሪፖርት ለቦርድ ማቅረብ።

# ክፍል አራት

# የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 18. የትምህርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

1/ በውድድሩ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው ያሳውቃል፤



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

2/ ሚኒስትሩ ከቦርድ የቀረበለትን አምስት ፕሬዚዳንታዊ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ቃለ መጠይቅ ያደርጋል፤(አባሪ 4 ይመልከቱ)

3/ ትምህርት ሚኒስቴር ከመግለጫ ጋር ከቦርድ ከቀረቡለት የመጨረሻ ሦስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንዱን በመምረጥ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚዳንት በመሰየም በህዝብ ተደራሽ በሆኑ ሚዲያዎች ያሳውቃል/ይፋ ያደርጋል፤

4/ አጠቃላይ የፕሬዚዳንቶች ምርጫ ሂደትን በቅርበት ይከታተላል።

19. የዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

1/ የእጩ ተወዳዳሪ አፈላላጊ እና የመራጭና መልማይ ኮሚቴዎችን ያዋቅራል፤ የውድድር ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፤

2/ የውይይትና የግምገማ መድረኮችን ያዘጋጃል፤ አጠቃላይ የውድድር ሂደቶችን በቅርበት ይከታተላል፤ ክፍተቶች ሲፈጠሩም እንዲስተካከሉ ያደርጋል፤

3/ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በሚለይበት ወቅት ብቃት ያለው ተወዳዳሪ ወይም በቂ ቁጥር ማግኘት ካልተቻለ፣ ውድድሩ እንዲቀጥል ወይም እንዲሰረዝ ውሳኔ ይሰጣል፤

4/ ቦርዱም ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ቃለ መጠይቅ ያደርጋል፤ (አባሪ 5 ይመልከቱ)

5/ የመልማይና መራጭ ኮሚቴው ለይቶ ከመግለጫና ከቃለ-ጉባኤው ጋር ያመጣቸውን አምስት ፕሬዚዳንታዊ ዕጩዎች ሙሉ ሰነዳቸውን በማያያዝ ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀርባል፤

6/ ሚኒስቴሩ መዝኖ የላካቸውን ተወዳዳሪዎች ቦርዱ በቃለ መጠይቅ በመገምገም፣ ከአምስቱ ሦስቱን እጩዎች በውጤታቸው ቅደም ተከተል በመለየት ከምክረ-ሀሳብ ጋር ፕሬዚዳንቱ እንዲሰየምለት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

7/ የምክትል ፕሬዚዳንቶችን ይሰይማል፤

8/ በውድድሩ ሂደት ላይ የቀረቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ምላሽ ይሰጣል።

20. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1/ ማስታወቂያ ለሚወጣባቸው ክፍት የኃላፊነት ቦታዎች ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሽፋን ባላቸው መገናኛ ብዙኃን፣ እንዲሁም በትምህርት ሚኒስቴር እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረ-ገጾችና ማህበራዊ ሚዲያዎች በግልጽ በማሳወቅ ለውጭ ሀገር ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጭምር ተደራሽ ያደርጋል፤(አባሪ 1 ይመልከቱ)



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

2/ በትምህርት ሚኒስቴር ለመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር አሰያየምን ለመደንገግ የወጣውን መመሪያ በተመለከተ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ግንዛቤ ይፈጥራል፤

3/ በስራ ላይ ያሉ ከፍተኛ አመራሮች የአገልግሎት ጊዜአቸውን ከመጨረሳቸው በፊት ተተኪ አመራሮች ምልመላና መረጣ እንዲካሄድ ማመቻቸትና ለቦርዱና ለትምህርት ሚኒስቴር ማሳወቅ፤

4/ ለኮሚቴዎቹ አስፈላጊውን የግብአት የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት የውድድርና ምርጫ ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን ይሰራል፤

5/ ዕጩ ተወዳዳሪው ለምዝገባ ሲመጣ ግለ-ታሪክ ማስረጃ፣ የትምህርት ማስረጃ፣ የዩኒቨርሲቲ መምህር ከሆነ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ያሳተማቸው የምርምር ሥራዎች፣ አርትኦት የተደረጉ አርቲክሎችን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን አያይዞ ማቅረቡን ያረጋግጣል፤

6/ እጩ ተወዳዳሪዎች ስትራቴጂክ እቅዳቸውን ሲያቀርቡ የሴኔት አባላትና ሲኒየር መምህራን ተገኝተው አስተያት እንዲሰጡ ያስተባብራል ፣ሂደቱ በሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ ያደርጋል።

## 21. ቅሬታ አቀራረብና አፈታት

1/ በአመራር አሰያየምና ምደባ ሂደት ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ቅሬታ ማቅረብ የሚችለው ምደባው በይፋ በተገለጸ በ15 ተከታተይ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ይሆናል፤

2/ ቦርዱ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ ምላሽ ይሰጣል፤

3/ ከፕሬዚዳንት እና ከምክትል ፕሬዚዳንት ምልመላ፣ መረጣ እና ምደባ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ቅሬታ በዩኒቨርሲቲው ቦርድ በሚሰጠው ምላሽ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማቅረብ ይችላል፤

4/ ሚኒስቴሩ ቅሬታው ከቀረበለት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ጉዳዮን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል፤

5/ ሚኒስቴሩ የሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## የኃላፊነት ቆይታ ጊዜ እና ከኃላፊነት ስለመነሳት

## 22. የቆይታ ጊዜ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

1/ የአንድ ጊዜ የፕሬዚዳንት የአገልግሎት ዘመን ለ6 (ስድስት) ዓመት ይሆናል።

2/ የስራ አፈጻጸሙ በአመት ሁለት ጊዜ (በየስድስት ወሩ) በሥራ አመራር ቦርድ በመገምገም የቆይታ አማካይ ውጤቱን መሰረት በማድረግ ቦርዱ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀርባል።

3/ ፕሬዝዳንቱ የቆይታ ጊዜውን አጠናቆ ለሁለተኛ ዙር ያለውድድር እንዲቀጥል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የተቋሙ አፈፃጸም በጣም ከፍተኛ እና አርአያ ሆኖ ሲገኝና በሥራ አመራር ቦርዱ ተገምግሞ ሲታመንበትና ለትምህርት ሚኒስቴር ቀርቦ ሲጸድቅ ይሆናል።

4/ የምክትል ፕሬዚዳንት የአንድ ጊዜ የአገልግሎት ዘመን ለ4 (አራት) ዓመት ይሆናል፣

5/ ምክትል ፕሬዝዳንት የአራት ዓመት ቆይታ ጊዚውን አጠናቆ ለሁለተኛ ዙር ያለውድድር እንዲቀጥሉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ምክትል ፕሬዚዳንቱ በሚመራው ዘርፍ ያለው አፈፃጸም በጣም ከፍተኛ እና በስራው አርአያ የሆነ ሲሆን፣ በፕሬዚዳንቱ አስተያየት ሰጪነት ለሥራ አመራር ቦርዱ ቀርቦ ሲጸድቅ ይሆናል::

## 23. ከኃላፊነት ስለመሰናበት

1/ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ከሃላፊነት ቦታው የሚነሳው በሚከተሉት ምክንያቶች ይሆናል፦

ሀ) በጤና እክል ምክንያት ስራውን ማከናወን ካልቻለ፤

ለ) በሁለት ተከታታይ የስድስት ወር ግምገማ ከከፍተኛ በታች ካመጣ፤

ሐ) በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ወይንም በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፤

መ) የጥቅም ግጭት ሲኖር እና በህግ ሲረጋገጥ፤

ሠ) የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በየስድስት ወሩ በሚካሄደው የፕሬዚዳንት የስራ ግምገማ መሰረት፣ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ እንዲሁም ህገ ወጥ ድርጊቶችን ፈጽሞ ሲገኝ ቦርዱ ፕሬዝዳንቱ ከኃላፊነት እንዲነሳ ለሚኒስቴሩ አስተያየት ሲያቀርብ።

2/ ቦርዱ ፕሬዝዳንቱ ከኃላፊነት እንዲነሳ የሚያቀርበው አስተያየት የዩኒቨርሲቲው ምልአተ ጉባኤው በተገኙበት በግልጽ ስብሰባ በሚደረግ ግምገማ በሚገኝ ተጨባጭ ማስረጃ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል።

3/ ሚኒስቴሩ ከቦርዱ በሚቀርበው የውሳኔ ኃሳብ ወይም የተፈጸመውን ከባድ ጥፋት ቦርዱ አቅርቧል ብሎ ካመነ ፕሬዚዳንቱን ከኃላፊነት የሚያነሳ ሲሆን ነገር ግን የቦርዱ የውሳኔ ሀሳብና የቀረቡለት ማስረጃዎች አሳማኝ ሆኖ ካላገኘው ሚኒስቴሩ በራሱ ጉዳዩን በማጣራት ይወስናል።

4/ ምክትል ፕሬዚዳንቱ በተከታታይ በየሶስት ወሩ በሚደረግ የሥራ ግምገማ የሥነ ምግባር ጉድለት ወይም ከሚጠበቀው በታች አፈጻጸም ካሳየ፣ በፕሬዚዳንቱ አስተያየት ሰጭነት ለቦርዱ ውሳኔ ይቀርባል።

5/ ቦርዱም ምክትል ፕሬዚዳንቱን ከኃላፊነት ለማንሳት የሚቀርብ አስተያየት የቦርድ አባላት እና የዩኒቨርሲቲው ማኔጅሜንት ምልአተ ጉባኤ በተገኙበት በሚደረግ ግልጽ ግምገማና በተጨባጭ ማስረጃ መሠረት በቦርዱ የሚወሰን ይሆናል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**24. የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ድርሻ ያለው ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።

**25. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

በቀድሞ መመሪያ ተወዳድረው የተመደቡ ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ኃላፊነታቸውን ያላጠናቀቁ አካላት፣ በአዲሱ መመሪያ መሰረት እንደተመደቡ ታስቦ የቆይታ ጊዜያቸው እስኪጠናቀቅ ድረስ በዚሁ መመሪያ ይመራሉ።

**26. ማሻሻያዎች**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትምህርት ሚኒስቴር ሊሻሻል ይችላል።

**27. የመመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

የትምህርት ሚኒስቴር፣ ሚኒስትር

2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## አባሪ-1፦ የአመራር ውድድር፣ መረጣና ሹመት ሂደት ናሙና መርሃ ግብር

ክፍት የአመራር የሥራ መደቡ ተለይቶ ለቦርዱና ለትምህርት ሚኒስቴር በደብዳቤ ከተገለጸ በኋላ የአመራር ክፍት የሥራ ቦታውን በውድድር ለመሙላት በሚከተለው መርሃ ግብር መሰረት የሚከናወን ይሆናል፤

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | የሚፈለገው ጊዜ | ሥራውን በኃላፊነት የሚፈጽመው |
|---|---|---|---|
| 1 | ክፍት የአመራር የሥራ ቦታውን ማስታወቂያ ማውጣት | ለ22 የሥራ ቀናት / ለ1 ሙሉ ወር | ከቦርድ ጋር በመመካከር የዩኒቨርሲቲው ሰው ኃብት አስተዳደር |
| 2 | የዕጩ አፈላላጊ ኮሚቴው ብቁ የሆኑ አመልካቾችን እንዲያፈላለግና እንዲያመለክቱ ማድረግ | ለ22 የሥራ ቀናት/ ለ1 (አንድ)ወር (ከማስታወቂያው ጋር በተመሳሳይ ጊዜ) | የዕጩ አፈላላጊ ኮሚቴው |
| 3 | የማስታወቂያ ጊዜው ካለቀ በኋላ የተወዳዳሪዎች ፋይል በማጣራት ብቁ የሆኑትንና ያልሆኑትን ለይቶ ማሳወቅና ብቁ የሆኑትን ለቀጣይ ሂደት በማስታወቂያ መለጠፍና ማሳወቅ፣ የውድድር ፕሮግራም ማውጣትና ማሳወቅ | እንደተወዳዳሪዎች ብዛት እስከ 1 (አንድ) ወር ድረስ | የመልማይና መራጭ ኮሚቴው |
| 4 | የተወዳዳሪዎች የትምህርትና የስራ ልምድን በመስፈርቱ መሰረት ውጤት መስጠት | ለ10 የሥራ ቀናት | የመልማይና መራጭ ኮሚቴው |
| 5 | እጩ ተወዳዳሪዎችን የስትራቴጂክ እቅድን እንዲያቀርቡ ማድረግ | እንደ ተወዳዳሪዎች ቁጥር የሚነሳ ሆኖ ለመነሻ የሚሆን ለ5 ቀናት፣<br>ስትራቴጂክ እቅድ ለማቅረብ ከ20 እስከ 30 ደቂቃ እንዲሁም ለኮሚቴው ጥያቄና መልስ አስተያየት 30 ደቂቃ በጠቅላላ 1 ሰአት ጊዜ ይኖራል። | መልማይና መራጭ ኮሚቴ |
| 6 | በውድድሩ አምስት ብልጫ ያመጡ ተወዳዳሪዎችን ለይቶ ለቦርዱ ማሳወቅ | በሦስት ቀናት ውስጥ | ውድድርና መራጭ ኮሚቴ |
| 7 | በውጤታቸው መሰረት ከተወዳዳሪዎች ቅሬታ መቀበል እና ምላሽ መስጠት | በ10 ተከታታይ የስራ ቀናት | ስራ አመራር ቦርድ |
| 8 | ቦርዱ የአምስት ብልጫ ውጤት ያመጡ ተወዳዳሪዎችን ከመልማይና መራጭ ኮሚቴ ከዝርዝር መግለጫ ጋር በመቀበል ለትምህርት ሚኒስቴር መላክ | በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ | ሥራ አመራር ቦርዱ |
| 9 | ትምህርት ሚኒስቴር የቀረቡለትን አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች እያንዳንዳቸውን ቃለ መጠይቅ በማድረግና የቃለ መጠይቁን ግብአት በማያያዝ ለቦርዱ መልሶ መላክ፣ | በአምስት ቀናት ውስጥ | ትምህርት ሚኒስቴር |



Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10 | ቦርዱ ከትምህርት ሚኒስቴር የተላከለትን የተወዳዳሪዎች መረጃ በማየትና እንደገና ተወዳዳሪዎችን የራሱን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከአምስቱ ውስጥ ሦስት ብቁ ተወዳዳሪዎችን በውጤታቸው ቅደም ተከተል መሰረት በመለየት ከምክረ ሀሳብ ጋር ፕሬዚዳንቱ እንዲሰምለት ለትምህርት ሚኒስቴር መላክ | በ10 የስራ ቀናት ቀናት ውስጥ | ሥራ አመራር ቦርዱ |
| 11 | ትምህርት ሚኒስቴር ከመግለጫ ጋር ከቀረበለት የሦስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ውስጥ አንዱን በመምረጥ መሾም፣ ለዩኒቨርሲቲና ለቦርድ ማሳወቅ | በ10 ቀናት ውስጥ | ትምህርት ሚኒስቴር |
| 12 | ለሚቀርቡ ቅሬታዎች መላሽ መስጠት | በ15 ቀናት ውስጥ | ትምህርት ሚኒስቴር |

## አባሪ 2፦ የአመራርነት የስራ ልምድ የትምህርት ዝግጅትና የአካዳሚክ ማዕረግ የነጥብ አሰጣጥ ማብራሪያ

### 2.1 ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚመጣ ተወዳዳሪ ፣ ለፕሬዚዳንትነት እጩ ተወዳዳሪ የሚሰጥ ነጥብ (ለትምህርት ዝግጅት እና ለአካዳሚክ ማዕረግ (30 በመቶ) )

| ተ.ቁ | የትምህርት ደረጃ | ትይዩ የአካዳሚክ ማዕረግ | የተሰጠ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ፒ.ኤች.ዲ ያለው | የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው | 30 |
| 2 | ፒ.ኤች.ዲ ያለው | የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው | 29 |
| 3 | ማስተርስ ዲግሪ ያለው | የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው | 28 |
| 4 | ማስተርስ ዲግሪ ያላት | የአካዳሚክ ማዕረግ ሳይጠበቅባት(ለሴት ተወዳዳሪ) | 28 |
| 5 | ፒ.ኤች.ዲ ያለው | የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው | 27 |
| 6 | ማስተርስ ዲግሪ ያለው | የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው | 26 |

### 2.2. የአመራርነት የሥራ ልምድ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለሚመጡ

| የአመራርነት ደረጃዎች | ክብደት | የአመራርነት የአገልግሎት ዘመን | | | | | | | | | | | ድምር ውጤት ከ30% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 12 | 11 | 10 | 9 | 8 | 7 | 6 | 5 | 4 | 3 | 2 | |
| ፕሬዚዳንትና በዚህ ደረጃ | 2.5 | | | | | | | | | | | | |
| ም/ፕሬዚዳንትና በዚህ ደረጃ | 2 | | | | | | | | | | | | |
| ኮሌጅ ዲንና በዚህ ደረጃ | 1.5 | | | | | | | | | | | | |
| ም/ዲን ፣ ም/ዳይሬክተርና በዚህ ደረጃ | 1 | | | | | | | | | | | | |
| ትምህርት ክፍልና በዚህ ደረጃ | 0.5 | | | | | | | | | | | | |



Federal Democratic Republic
Ministry of Educ

በፕሬዚዳንትነት እና በዚህ ደረጃ ለተያዘ አገልግሎት በ2.5፣ በም/ፕሬዚዳንትነት በዚህ ደረጃ አገልግሎት በ2፣ በኮሌጅ ዲንና በዚህ ደረጃ ለተያዘ አገልግሎት በ1.5፣ በምክትል ኮሌጅ ዲንነት ወይም በአካዳሚክ ዘርፍ በምክትል ዳይሬክተርነት ለተያዘ አገልግሎት በ1 እና ለትምህርት ክፍል ሃላፊና በዚህ ደረጃ ለተያዘ አገልግሎት በ0.5 ክብደት እየተባዛ ውጤቱ የሚሰላ ይሆናል። የአመራርነት የሥራ ልምድ ሲያዝ ከከፍተኛ አመራርነት ልምድ ወደ ዝቅተኛ እየተያዘ 30 ነጥብ እስከሚያገኝ ድረስ መያዝ ይኖርበታል።

- **ምሳሌ 1፦** አንድ ለፕሬዚዳንትነት ውድድር እጩ የሆነ ተወዳዳሪ 12 ዓመት የፕሬዚዳንትነት፣ 8 ዓመት የም/ፕሬዚዳንትነት እና 5 ዓመት የኮሌጅ ዲንነት ወይም በአካዳሚክ ዳይሬክተርነት የአመራር የሥራ ልምድ ቢኖረው ሊያገኝ የሚችለው ውጤት በፕሬዚዳንትነት ያለው የአገልግሎት ዘመን 12 ዓመት (12 * 2.5 = 30) ይሆናል ማለት ነው። ምክንያቱም በፕሬዚዳንትነት ብቻ የሰራበት የፕሬዚዳንትነት የስራ ልምድ ብቻ ከፍተኛውን ውጤት ማግኘት ስለቻለ በሌሎች የአመራርነት መደብ ላይ የሰራበትን አንይዝለትም ማለት ነው።

- **ምሳሌ 2፦** አንድ አመራር ለፕሬዚዳንትነት የአመራር መደብ የተወዳደረ በፕሬዚዳንትነት 3 ዓመት፣ በምክትል ፕሬዚዳንትነት 8 ዓመት፣ በኮሌጅ ዲንነት ወይም በአካዳሚ ዘርፍ ዳይሬክተርነት 3 ዓመት፣ በምክትል ዲንነት ወይም አካዳሚክ ዳይሬክተርነት 4 ዓመት እና በትምህርት ክፍል ኃላፊነት 8 ዓመት የአመራርነት ልምድ ቢኖረው የአመራር ልምድ ነጥቡ ሊሆን የሚችለው፦

  (3 * 2.5) + (8 * 2) + (3 * 1.5) + (4 * 1) + (8 * 0.5) = 36 ነው። ሆኖም ለአመራርነት ልምድ የተሰጠው ከፍተኛው ክብደት 30 ነጥብ ስለሆነ ለተወዳዳሪው ሙሉ ነጥብ 30 በመስጠት ትርፉ 6 ነጥብ አይያዝም ማለት ነው።

3. ከኢንዱስትሪ ለሚመጣ ተወዳዳሪ የአመራርነት የሥራ ልምድ ውጤት አሰጣጥ

| የአመራርነት ደረጃዎች | ክብደት | የአመራርነት የሥራ ልምድ | | | | | | | | | ድምር ውጤት ከ30% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 10 | 9 | 8 | 7 | 6 | 5 | 4 | 3 | 2 | |
| በበላይ ኃላፊነት | 3 | | | | | | | | | | |
| በከፍተኛ ኃላፊነት | 2.75 | | | | | | | | | | |
| በዋና ዳይሬክተር፣በም/ዋና ዳይሬክተር፣በመሪ ሥራ አስፈፃሚ፣በዳይሬክቶሬት ጀነራል እና በዚህ ደረጃ የሰራ | 2.5 | | | | | | | | | | |

ለአመራርነት መደቡ አግባብነት ላለው የአመራርነት ልምድ ውጤት የሚሰጠው ለእያንዳንዱ የአመራርነት የአገልግሎት ጊዜ ሆኖ በበላይ ኃላፊ እና በዚህ ደረጃ ለተያዘ አገልግሎት በ3፣ በከፍተኛ ኃላፊነት እና በዚህ ደረጃ ለተያዘ አገልግሎት በ2.75፣ በዋና ዳይሬክተር፣ በም/ዋና ዳይሬክተር፣ በመሪ ሥራ አስፈፃሚ፣ በዳይሬክቶሬት ጀኔራል እና በዚህ ደረጃ ለተያዘ አገልግሎት በ2.5 ማባዣ ክብደት እየተባዛ የሚቀመጥ ይሆናል። (ከላይ በምሳሌ 2 ላይ በተቀመጠው መሰረት መስራት ይቻላል፡)

አባሪ 3

መልማይና መራጭ ኮሚቴው ተወዳዳሪዎችን ከ100% አወዳድሮ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ አምስት ዕጩዎችን በመለየት ለሥራ አመራር ቦርድ ያቀርባል። ቦርዱም ከኮሚቴው የተላከለትን የተወዳዳሪዎች ውጤት በቅደም ተከተሉ መሠረት በማዘጋጀትና አስፈላጊ ሰነዶችን በማያያዝ ለቀጣይ ግምገማ  ለትምህርት ሚኒስቴር ይልካል።

አባሪ 4

ትምህርት ሚኒስቴርም ከሥራ አመራር ቦርድ የተላኩለትን አምስት ተወዳዳሪዎች እስከ 10% የሚደርስ የቃለ መጠይቅ ክብደት በመስጠት ይመዝናል። በመጨረሻም ከቃለ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ከምልመላ ኮሚቴው ከተላከው ውጤት ጋር በመደመርና ወደ 100% በመለወጥ፣ እንደየ ውጤት ቅደም ተከተላቸው አረጋግጦ ለሥራ አመራር ቦርድ መልሶ ይልካል።

**ምሳሌ** 1. *መልማይና መራጭ ኮሚቴው ተወዳዳሪውን* ከ100% *አወዳድሮ* 85 *ነጥብ ቢሰጠው እና ትምህርት ሚኒስቴር ደግሞ ከኮሚቴው በቀረበለት የዕጩው ውጤት ላይ* ከ10% *የራሱን ቃለ-መጠይቅ አድርጎ* 7 *ነጥብ ቢጨምር፣ የተወዳዳሪው የተጣመረ ድምር ውጤት* ከ110% *ውስጥ* 92 (85 + 7) *ይሆናል። ሆኖም ይህ የውጤት መረጃ ወደ ቦርዱ ተመልሶ ከመላኩ በፊት ወደ* 100% *መለወጥ ስላለበት፣ የተገኘውን ድምር ውጤት* በ100 *አባዝቶ* ለ110 *በማካፈል* (92 * 100 / 110) *የመጨረሻውን ውጤት* 83.63% *ማግኘት ይቻላል። (ይህ ምሳሌ ለአባሪ 5ም በተመሳሳይ ያገለግላል)*

አባሪ 5.

ቦርዱ በትምህርት ሚኒስቴር ተገምግሞ የተላከለትን የተወዳዳሪዎች መረጃ በማየትና እንደገና ተወዳዳሪዎችን የራሱን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከአምስቱ ውስጥ ሦስት ብቁ ተወዳዳሪዎችን በውጤታቸው ቅደም ተከተል መሰረት በመለየት ከምክረ ሀሳብ ጋር ፕሬዚዳንቱ እንዲሰየምለት ለትምህርት ሚኒስቴር ይልካል።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education